የ Covid-19 ክትባት
ለስደተኛ ማህበረሰብ አባላት መብቶቻችዎን ይወቁ

- የዜግነት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ክትባቱ በአሜሪካ ውስጥ ለሁሉም ሰው ያለ ምንም ወጪ ይገኛል፣ (ሰነድ የሌሎት ቢሆኑም እንኳን)። የኢንሹራንስ ካርድ ሊጠየቅ ይችላል ግን ክትባት ለመውሰድ አያስፈልግም።

- ክትባት ለመውሰድsocial security number (የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር) አያስፈልግም። አንድ አቅራቢ social security number ከጠየቀዎት እና እርስዎ ከሌልዎት ወይም እሱን ለማጋራት ምቾት ካልተሰማዎት፣ እርስዎ የለኝም ወይም ለማጋራት ምቾት አልተሰማኝም ብለው መልስ መስጠት ይችላሉ።

- ክትባትዎን ለማግኘት መታወቂያ ሊጠየቁ ይችላሉ። የግዛት መታወቂያ/የመንጃ ፈቃድ ከሌልዎት በአሁን አድራሻዎ ደብዳቤ፣ መግለጫ፣ ወይም የፍጆታ ሂሳብ እንዲያቀርቡ ወይም በዋሽንግተን ግዛት እንደሚኖሩ ወይም እንደሚሰሩ የሚያረጋግጥ ከሚያውቅዎት ቤተ ክርስቲያን፣ ድርጅት፣ ወይም አቅራቢ የተላከ ደብዳቤ እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ።

- የ Centers for Disease Control and Prevention (የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከያ ማዕከላት) እና የአሜሪካ Department of Health and Human Services (የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ) የግል መረጃዎች ለህዝብ ጤና አገልግሎት ብቻ እንደሚውሉ አፅንዖት ሰጥተዋል። የኢሚግሬሽን አስፈጻሚዎችን ጨምሮ የግል መረጃዎች ለፍትሐብሔር ወይም ለወንጀል ክስ ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም።

- ክትባቱን መውሰድ በምንም መንገድ እንደ የህዝብ ክፍያ አይቆጠርም።ክትባቱን መጠቀሙ የመኖሪያ ፈቃድ እና/ወይም የዜግነት ሁኔታ ለማግኘት ማንኛውንም ዕድል አያደናቅፍም።

- ክትባት ለማግኘት ማንም ሰው ስለ ስደተኛነት ሁኔታዎ ሊጠይቅ አይገባም ነገር ግን በማንኛውም ጊዜ ስለ ስደት ሁኔታዎ ከተጠየቁ፣ ዝም የማለት መብት አለዎት።

- የስደት ሁኔታው ምንም ይሁን ምን ማንኛውም ሰው ክትባቱን መውሰድ ይችላል። ክትባቱን ለማግኘት የስደት ሁኔታዎን ማረጋገጫ ማቅረብ አይጠበቅብዎትም።

ልዩ ምስጋና ለ Legal Counsel for Youth and Children (LCYC፣ ለወጣቶች እና ሕፃናት የሕግ አማካሪ) እና ለ Northwest Health Law Advocates (NoHLA፣ የሰሜን ምዕራብ የጤና ሕግ ተሟጋቾች)

ይህ ሰነድ በ WA DOH (የጤና መምሪያ) ተረጋግጧል

Washington State Department of Health

WASHINGTON IMMIGRANT SOLIDARITY NETWORK